*Moresh Amhara Civic Organisation In Europe*
የሞረሽ አማራ ሲቪክ ማህበር በአውሮፓ

ህዳር 2017

# <u>የብአዴን የጸረ ሞረሽ ዘመቻ</u>

ሞረሽ ዘሩ በመጥፋት ላይ ላለ የአማራ ህዝብ የመሰባሰቢያ ጥሪ ነው።
ጥሪውካልተሰባሰብንና ካልተደራጀን እንጠፋለን ነው።
በሞረሽ ስር የቆሙየአማራ ልጆች ከ 5ዓመታት በፊት ይህንን
ጥሪ ሰምተውየተሰባሰቡት በዘሩ እንዲጠፋ በወያኔ ትግሬ
የተፈረደበትን የአማራ ወገናቸውን ለመታደግ ነበር። ዓላማውም
የዘር ምንጠራውን ለመመከት የሚችለውአማራውእራሱ እንጂ ሌላ ረዳት
እንደሌለው አውቆ እንዲደራጅ ለመቀስቀስ፣ ይህንን በተጠናና
የረጅምጊዜ ተይዞለት በመካሄድ ላይ ያለን የዘር ፍጂት ለዓለም
ህብረተሰብ ለማሳወቅ፣ የህዝቡንም መልሶ የማጥቃት ትግሉን
ለመርዳትና ከዓለምዙሪያ እራዳታ ለመሻት፣ የትግሬ ወያኔንና
የተባባሪዎቹን ማንነት በመመዝገብ ለታሪክና ለፍርድ ለማቅረብ
የተቋቋመየብዙሀን ድርጂት ነው። ሞረሽ ከዚህ ውጪሌላ የተቋቋመበት
ምንም ዓላማየለውም።
አባላቱም ለዚህ ዓላማ እውን መሆን ብቻ ተባብረውየቆሙናቸው።
አባላቱ ከዚህ ሰእባዊ አቋማቸውባለፈ የተለያየ የፖለቲካ
አመለካከትን የማስተናግዱናቸው። በተለያዩ የፖለቲካ ድርጂቶች
ስር ተጠልለው የአማራውን የነገ የሀገራዊ የስልጣን ጥቅሙን
በሚመለከት የሚታገሉ ግለሰቦችንምቢያካትት አያስደንቅም።
ሞረሽ የአማራውየብዙሀን ድርጂት እንደመሆኑ የአማራውህዝብ እንደ
ህዝብ ከጥፋት እንዲድን እንደ ኢትዮጵያዊነቱ ደግሞየሀገሩ ባለቤት
እንዲሆን ያስተምራል፣ ይቀሰቅሳል፣ እንዲደራጅምያበረታታል፣

ባንክ(Bank):
**MWACO in Europa**
IBAN: NL75SNSB 0870725904
**BIC SNSBNL2A**

ኢሜል(Email):
ለመረጃ፤ editor@moreshinfo.com
ለክፍያ **bejerond@gmail.com**
**Chamber of Commerce registration no. 59635975**

የተደራጁትም እንዲተባበሩና በአንድ የተጠናከረ የፖለቲካ ድርጂት ዙሪያ እንዲመጡ ይመከራል። በመሰረቱ ድርጂት በተፈጥሮው ተበታትነው ያሉና የባለጊዜው ተጠቂ የሆኑ አቅመደካሞችን አሰባስቦ እምቅ ሀይላቸውን አውጥተው መልሰው የማይበገሩ ሀያላን እንዲሆኑ የማድረግ ችሎታው የተፈተነ ነው። ድርጂት የሀይል ምንጭ ስለመሆኑ ወያኔ ጥሩ ምሳሌ ነው። ወያኔ በአማራው ላይ ዛሬ የምናየውን መጠን የለሽ ግፍን ማዝነብ የቻለው በመደራጀቱ ነው። ሌላ ሚስጥር የለውም።

ይህንን ወደር የለሽ የወያኔን ጥፋት ልንቀለብስ የምንችለው በአንድ መሳሪያ ብቻ ነው። በድርጅትና በመደራጀት!! ዛሬ ለአማራው ህዝብ የቀረበውና መመለስ ያለበት የመደራጀት ጥያቄ መሆኑም የሚታይን ነው። ሞረሽ የአማራ ህዝብ የበቃ የፖለቲካ ድርጂት ስር ተጠቃሎ በሀገሩ የፖለቲካ ተሳትፎ ማድረግ ሲችል የሚጠፉ ድርጂት የሚመስላቸው ብዙ ናቸው። ሞረሽ በጊዜ መሀል የተገደበ ድርጂት አይደለም። የአማራ ህዝብ እንደ ህዝብ እስከኖረ ጊዜ ድረስ የሚኖር እምባ ጠባቂ ድርጂቱ ነው። ሞረሽ በአማራ ህዝብ ላይ ዛሬ በመድረስ ላይ ያለ ጥፋት እንዳይደገም ለማድረግ ህዝቡ በኢኮኖሚው የደረጀ፣ በማህበራዊ አቋሙ የጠነከረ፣ በፖለቲካ ግንዛቤው የዳበረ አመለካከት ባለቤት እንዲሆን ከጎኑ ቁሞ የሚታገል የብዙሀን ድርጂት ነው። ይህንን ተለኮውን የሚያከናወኑ ውካሉት የአማራና ሌሎች በሀገሪቱ አንድነትን ከሚያምኑ የፖለቲካ ስብስቦች ጋር በሚፈጥረው ግኑኝነት ላይ ተመስርቶ ይሆናል። የአማራውን ጥቅም ለማስተናገድ ፈቃደኛ ለሆኑት ድጋፉን ይለግሳል። የአማራውን ጥቅም ለሚጋፉት ድጋፉን ይነሳል። ይህን ተጽእኖ ለመፍጠር የሚያስችለውን የድርጂትና የገንዘብ ሀይል ማሰባሰብ የዛሬ ስራው ይሆናል።



ኢሜል(Email):
ለመረጃ፤ editor@moreshinfo.com
ለክፍያ **bejerond@gmail.com**

*Moresh Amhara Civic Organisation In Europe*
**የሞረሽ አማራ ሲቪክ ማህበር በአውሮፓ**

ይህንን የሞረሽን የዘላቂ ግብ የተገነዘበው ተላንት የወያኔ ባንዳ የንቃተ ህሊናቸው በዝቅተኛ ደርጃ ላይ ያሉትን የአማራ ወገኖቻችንን በተለያዩ ጥቅማጥቅሞች በመያዝ በሞረሽ ላይ ከፍተኛ የሆነ ዓላማውን የማጠልሸት ዘመቻ እየተካሄደ መሆኑ የሚታይ ነው። ይህ ዘመቻ የሚካሄደው በወያኔ ሰራሹ በብአዴን መሆኑም የአደባባይ ሚስጢር ነው። ብአዴን ይህንን ተግባር እንዲፈጽምለት በአማራ ማህበረሰባችን ውስጥ ደካሞችን አስርጎ አስገብቷል። በሶሻል ሚዲያ የብአዴንን ተክለ ሰውነት አድሶ ለማቅረብ የሚሰራ ትልቅ ሀይል አሰማርቷል።

በአማራው ድርጅቶች ውስጥ አስርጎ ያስገባቸው የስራ ድርሻ ውስጥ “ሞረሽ የፖለቲካ ድርጅት ነው አትጠጉት” የሚለው ዘመቻ ዋናው ነው። ብአዴን ይህንን የሚያደርገው በአማራ የመደራጀት ጥረት ውስጥ የርስበርስ ጦርትን ለመለኮስ ነው። ያማራ ልጆች መሀል የማያልቅ የጎንዮሽ ትግል በመጫር ወደማያባራ ግጭት ውስጥ ለመክተት ነው። በመጨረሻም የአማራውን ጅምር የመደራጀት ጥረት በለጋው ለመንቀል መሆኑ መያዝ አለበት።

ዛሬ በሞረሽ ስር የተሰባሰብን ወገንተኝነታችን ለአማራው ህዝብ ህልውና መጠበቅና ለናት ሀገራችን አንድነት መጽናት ነው። ድርጅታችንም የብዙሀን ድርጅት እንጂ የፖለቲካ ድርጅት አይደለም። ይህንን ሀቅ ለማጠልሸት የሚሰሩ የወያኔ ሰራሹ የብአዴን መለክተኞችና ሃሜተኞች ብቻ እንደሆኑ እንዲታወቅ ያስፈልጋል። የሞረሽ ተልእኮ ረጅም፣ አመለካከቱም ከፖለቲካ ድርጅት ባሻገር የሆነ ሆደሰፊ የብዙሀን ድርጅት ነው።

ዛሬ ሞረሽ በማሳወቅ ስራው ብዙ ገፍቶ በመሄድ የአማራ ድምጽ ራዲዮን አቋቁሟል። እየተጠናከረ ሲሄድ ደግሞ የተለቪዥን ጣቢያ እስከ

ባንክ(Bank):
**MWACO in Europa**
IBAN: NL75SNSB 0870725904
**BIC SNSBNL2A**

ኢሜል(Email):
ለመረጃ፤ editor@moreshinfo.com
ለክፍያ **bejerond@gmail.com**
**Chamber of Commerce registration no. 59635975**

*Moresh Amhara Civic Organisation In Europe*
**የሞረሽ አማራ ሲቪክ ማህበር በአውሮፓ**

ማቋቋም የሚደርስ ህልም የሰነቀ ድርጇት ነው። ጠላቶቻችን እንደሚያስወሩብን ሳይሆን እነዚህ የማሳወቅ መሳሪያዎች የሁሉም አማራ የፖለቲካ ስብስቦች መገልገያዎች ናቸው። ዛሬም የአማራ ሬዲዎን በመስራት ላይ ያለው ይህንኑ ነው።

በሞረሽ እምነት የአማራው ዋና ጠላቱ ከራሱ ወስጥ የሚወጣው የአማራው ባንዳ ነው። ለዛሬ ድክመቱም ምክንያት ይህ የጥፋት ሀይል በሚፈጥረው የወስጥ መመሰቃቀል ነው። ትልቁና ልንዋጋው የሚገባ አደጋ ይህንን የተደገሰልንን የርስ በርስ ሽኩቻን ነው። ይህንን የወስጥ ሴራን ካልተዋጋንና እነሱ በሰሩልን ወጥመድ ወስጥ ገብተን እርስ በርስ ትግል ከተያዝን ጠላት ወያኔ የአማራን ህዝብ በራሱ ድክመት ድል ነሳው ማለት ይሆናል። የህዝባችንም የህልውና ትግል ያከትማል ። ህዝባችንም እንደ ህዝብም ይጠፋል። ሞረሽ ይህንን አደጋ የተገነዘበ ድርጇት ነው። በመሆኑም በምንም መንገድ ለወያኔ ባንዳ ሴራ እጁን ስጥቶ ከወገን ድርጇቶች ጋር እንኪያ ስላንቲያ ወስጥ አይገባም። ሌሎችም ምሳለሌውን እንዲከተሉት ሳይታክት ጥሪውን ያስተላልፋል። ሁሉም ያማራ ድርጇቶች ይህንን እንደ ድርጇታቸው የመታገያ መመሪያቸው ያደርጉት ዘንድ ሳይታክትና ሳይደክም ከማስታወስ ወደኋላ አይልም።

ሞረሽ ለአማራው ህልውና መጠበቅ የተደረገ ጥሪ ነው!!!
ሞረሽ የአማራው ህዝብ እምባ ጠባቂ የብዙሀን ድርጇቱ ነው!!!
አንድ አማራ ለሁሉም አማራ ሁሉም አማራ ለአንድ አማራ
ዘብ ይቁም !!!

ባንክ(Bank):
**MWACO in Europa**
IBAN: NL75SNSB 0870725904
**BIC SNSBNL2A**

ኢሜል(Email):
ለመረጃ፤ editor@moreshinfo.com
ለክፍያ **bejerond@gmail.com**
**Chamber of Commerce registration no. 59635975**